# አፍሪቃ

በአውሮፓ- አሜሪካ የንግድ አደባባይ
ተሸጠን ተገዝተን በአረብ ባሪያ ፈንጋይ
በደም ግብር ትግል ከባርነት ወጥተን
ስብዕና የሌለው ነፃነት አግኝተን
የወርቅ ማዕድን የአልማዝና ኮባልት
ዩራኒየም መዳብ እምቅ ነዳጅ ዘይት
አመንጭዎች ሆነን ሸቀጥ የትርፍ ዕቃ
ሀብት የሞላን ድሆች ተገኘን ነን አፍሪቃ።
የነጭና ቢጫ ዘር የበላይነት
የአረቡን ዕቡይ ትዕቢትና ትምክህት
አንገት የሚያስደፋ ስልጣኔና ዕውቀት
የአህጉር ሃይል ሆነን እስካላስጨነቅናት
ባለም አታወቀንም እኛ እንኳ ብናውቃት።

ነሃሴ 2003

አብርሃም በየነ